በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የተሰጠ መግለጫ

ግንቦት 14 ቀን 2007ዓ.ም

***<u>የወያኔ/ኢህአዴግ ተግባር ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ።</u>***
***<u>በስብሰባ ጋጋታና በባዶ ፐርፖጋንዳ እንዳንፈታ ትግሉ ይፋፋም!</u>***

የችግራችን ቀጣይ ክስተቶች ለትምህርተ ሥርዓቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሽቆልቆልና የውድቀት ጠርዝ መድረስ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ባይካድም ያለፉትን መንግሥታት በመኮነን ከምንም በላይ ራሱን የለውጥ ሐዋሪያና የዕደገት ተምሳሌት አድርጎ የሚቆጥረው ወያኔ/ኢህአዴግ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የትምህርት አመራር ከመስጠትና ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ ይበልጥ ውስብስብና ሊፈቱ ከማይችሉበት ደረጃ አድርሷቸዋል።
በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተማሪዎች በመምህራን እጥረት፣በመማሪያ ክፍሎች፣ በማስተማሪያ መጻሕፍትና በሌሎችም የትምህርት ግብአቶች እጥረት የተነሳ የተሟላ ትምህርት የማያገኙበት፣ ተማሪዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ ተስፋ የቆረጡበት ፣ ፈተና በአንድና በሁለት ደቂቃዎች ሰርተው የሚያጠናቅቁበት፣ ጭራሹን ትምህርታቸውን ለማቋረጥ የሚገደዱበት ወቅት ስለሆነ ትምህርት ቀውስ ውስጥ ገብቷል።
የዚህ ቀውስ አንዱ ማሳያ ሊሆን የሚችለው ወያኔ/ኢህአዴግ በሶስት ምድብ አመቻችቶ የማደናገሪያ /የማጭበርበሪያ አጀንዳዎቹን ለማስፈጸም የሚሞክርበትን አካሄድ ቀጥሎ እንመልከት፡-
<u>ከመምህራን ጋር</u> ፡-በአንዳንድ አካባቢዎች በህዳር ወር 2007ዓ.ም መጀመሪያ ሳምንት በተደረገ የመምህራን ስብሰባ ከ2006ዓ.ም በፊት በነበሩት አመታት ትምህርታቸውን ያቋረጡ ተማሪዎች እስከ ህዳር ወር መጨረሻ 2007ዓ.ም ድረስ ትምህርት ቤት እንዲገቡ የሚል ሐሳብ በወያኔ ካድሬዎች ይቀርባል።ለዚህ የተሰጠው ምክንያት የምዕተ ዓመቱ (የሚሊኒየሙ) የልማት ግብ በዚህ በያዝነው አመት ስለሚጠናቀቅ አሁን በመማር ላይ ያሉት መማር ከሚገባቸው ተማሪዎች ቁጥር ያነሰ በመሆኑ ያቋረጡትን "በቅስቀሳ " በማምጣት ከመስከረም 2007ዓ.ም ጀምሮ እየተማሩ ካሉት ጋር እኩል ማድረስና የምዕተ ዓመቱን " ትምህርት ለሁሉም" የሚለውን ግብ ማሳካት በሚል የቀረበ አጀንዳ ነበር።
በዚህ አጀንዳ ላይ የመማር ተግባራቸውን አቋመው ለዓመታት ከትምህርት ገበታቸው ተለይተው የቆዩ ተማሪዎችን የትምህርት መጀመሪያ ዓመት ካለፈ ከወራት በኋላ መቀበል ማለትም እስከ ህዳር ወር 2007ዓ.ም ያልተማሩትን በምን ተአምር ትምህርት እንዲያገኙ ይደረጋል? ከትምህርት ተለይተው የቆዩት ተማሪዎች ለተለያዩ ደባል ሱሶች የተጋለጡ ሊኖሩ ስለሚችሉ በነባሮቹ ላይ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር የትምህርት ቤቶችን ድሲፕሊን ይጎዳል በሚል መምህራን ተቃውመውታል።ሥርዓቱ ፊቱ ላይ የሚታየው የአፈጻጸም ሂደት የውጭ ርዳታ ማግኘትን ትኩረት ሰጥቶ ንዋይ መሰብሰብ ዋናው ዓላማ ሆኖ ትምህርቱና ትውልዱ እንዲሞቱ ተፈርዶባቸዋል በማለት አስተያየት እየሰጡ ስብሰባውን ረግጠው እስከመውጣት ደርሰዋል።
ከዚህ በመቀጠል በታህሣሥ ወር መጨረሻ 2007ዓ.ም በአማራ ክልል የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች ለ3 ቀናት የሚቆይ

- የተሀድሶ መስመርና የኢትዮጵያ ህዳሴ
- የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና በትግሉ የተገኙ ውጤቶችና ተግዳሮቶች
- የ2007ዓ.ም የትምህርት ንቅናቄ ሰነድ በሚሉ አጀንዳዎች ስልጠና የሚል ስያሜ ተሰጥቶት የስልጠናው ዓላማ መምህራንና ተማሪዎች በተጀመረው የልማትና የመልካም አስተዳደር ላይ ግልጽነት እንዲኖር ለማድረግ የሚል ሆኖ ቀጥሎ ያሉት ንዑስ ዝርዝሮች ተካተዋል።

1. የተጀመሩትን ኢከኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ለውጦች ከዳር ለማድረስና የአጋጠሙ ተግዳሮቶችን ፈትሾ የአገራችንን የተሀድሶ ጉዞ ከትምህርት ማህበረሰብ ጋር ያለውን ፋይዳ ለመመዘን፣
2. ልማታዊ አስተሳሰብ የተሀድሶው መነሻ በመሆኑ ሁላችንም ልማታዊ አስተሳሰብ እንድንይዝ ለማስቻል፣
3. የህዳሴው የጉዞ ደረጃና መድረሻ ምን እንደሆነ ለማስገንዘብ፣

P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

4. ችግሮችን መለየትና ለውጡን በጠራ አቅጣጫ ለመምራት የሚያስችሉ ግብአቶች ለማግኘት፣
5. የተደራጀ የትምህርት የልማት ሠራዊት ግንባታ ለትምህርት ጥራት የማይተካ ዓላማ አለው፣ስለሆነም በተበታተነ አደረጃጀት ጥራት ማምጣት ካለው ፋይዳ ጋር ለመገምገም፣
6. የ2007 ዓ.ም የትምህርት በጀት የዕድገትና የልማት ዕቅዱ ማጠቃለያ ስለሆነ የቀሩንን ለይተን ርብርብ ለማድረግ ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት ወሳኝ ስለሆነ ፣
7. የአገራችን የተሀድሶና የህዳሴ ጉዞ የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች አውቆ ርብርብ ለማድረግ እንዲያስችል ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑ በካድሬዎች ተነግሮ አስፈላጊ ነው ወይስ አይደለም የሚል ጥያቄና የአስተያየት ሀሳብ ከራሳቸው ከካድሬዎች ይነሳል።

ለነዚህ ከላይ ለተዘረዘሩት በትምህርት ስልጠና ስም በወያኔ ለቀረበው የፖለቲካ አጀንዳ የመምህራን መልስ ይህ አቀራረብ በየቀኑ ከምንሰማው ፕሮፓጋንዳ የተለየ አይደለም፣ ሰነዱ የስልጠና ይዘት የለውም፣ለስልጠናም የሚያግዝ የማቴርያል ( የቁሳቁስ) አቅርቦት የለም፣ እንዲያውም በትምህርቱ የንፍቀ ዓመት ( የሴምስተሩ አጋማሽ ወቅት) መዘጋጀቱ የትምህርትን ሂደት የሚጎዳ ስለሆነ አስፈላጊ አይደለም የሚል በመሆኑ ውዝግብ ተፈጥሮ ስልጠና ተብዬው ለግማሽ ቀን ያህል ተቋርጦ ከቆየ በኋላ ከመምህራን ፍላጎት ውጪ በካድሬዎች ጫና ሊቀጥል ችሏል።
ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከትምህርቱ ጉዳይ ጋራ በማጣመር የቀረቡት አንዳንድ ትምህርት ነክ አጀንዳዎች ዓላማቸው የወያኔን የተሳሳተ የፖለቲካ መሰመር ጥሩ ገጽታ ለማላበስ የቀረቡ ናቸው። ሐሳብን በነፃነት የመግለጽና የመደራጀት መብት ፣ የብሔርና የሃይማኖት እኩልነት ተረጋግጧል በማለት የውሸት ድስኩሩን በሰብሰባዎቹ ወቅት አቅርበዋል።እንዲሁም ከአማራ ክልል የተወሰደ መሬት የለም፣የድሮዋን ኢትዮጵያ የተሻለች አድርጎ ማቅረብ፣ የአማራ ሕዝብ እንደተዋረደና ዝቅ ተደርጎ እንደሚታይ ማቀንቀን፣ ፌዴራሊዝም ኢትዮጵያን ለማፈራረስ የታቀደ ነው ማለት ፣ የአንድ ብሔር የበላይነት እንዳለ አድርጎ መቀስቀስ የትምክህትና የጠባብነት መግለጫዎች ናቸው በማለት የወያኔ ካድሬዎች በሕዝብ ላይ የፈጸሙትንና እየፈጸሙ ያሉትን እውነት ክደዋል። መቼ ወያኔና እውነት ይታዋወቃሉ?
በሀይማኖት ስም የፖለቲካ አጀንዳ ይዞ ወደ ሕዝብ መግባትና ሕገመንሥቱን መቃወምና ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት አንድ አገር፣ አንድ ሀይማኖት፣ በመጅሊሶቻችን መሪዎቻችንን እንዳንመርጥ መንግሥት ጣልቃ እየገባ ነው ፤የሸሪአ ሕግ መመስረት አለበት ፤ የእስላም መንግሥት እናቋቁማለን ፤ በትምህርት ቤቶች መስገጃ ቦታ ይፈቀድልን የመሳሰሉት በክርስትናና በእስልምና እምነት ተከታዮች የሚንፀባረቁ የአክራሪነት መገለጫዎች ስለሆኑ በትግል መፍታት ይገባል ተብሎ በካድሬዎች በኩል ለቀረቡት አስተያየቶች የመምህራኑ መልስ ለካድሬዎች የቀና አልነበረም። ቀድሞውንም በስልጠናው ይዘትና አካሄድ ደስተኛ ያልነበሩት መምህራን ባንድ ድምፅ ተቃውሞቻቸውን በማስተጋባት እኛ አንድ ነን፣ አትከፋፍሉን፣አንከፋፈልም በማለት በጩኸት፣ በፉጨት፣ በሞባይል ወኔ ቀስቃሽ የሆኑ የቀረርቶና የሽለላ ዜማዎችን በማሰማት የካድሬዎችን የውሸትና የተንኮል ፕሮፖጋንዳ ጆሮ ሳይሰጡ በወቅቱ መምህራን ያሳዩት ተቃውሞና የትግል ተነሳሽነት የሰርዓቱን ውድቀት አይቀሬነት አመላካች ነበር።
እንዲሁም በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች በትምህርትና በመምህራን ላይ የሚፈጸመው በደል ዘርፈ ብዙ ነው። በደቡቡ የአገራችን ክፍል የእርከን ጭማሪ ለርዕሳነ መምህራንና ለሱፐርባይዘሮች ተፈቅዶ ለመምህራን የተከለከለ መሆኑን ለተለያዩ የዞን ት/ቤቶች አሰተዳደር ከደቡብ የትምህርት ቢሮ የተለከው ደብዳቤ ያሳያል። ወያኔ ለይስሙላው ምርጫ መጠቀሚያ ለማድረግ የድርጅቱ አባል የሆኑትን መምህራን በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ በትምህርት ሰዓት ስብሰባ በማካሄድ በትምህርት ላይ በደል እየፈጸመ ይገኛል። በ11/07/2007 በሀድያ ዞን ውስጥ በዋቸሞ መሰናዶ ት/ቤት ለወያኔ የምርጫ ድራማ ለ25 የወያኔ/ኢህአዴግ አባል መምህራንና ሰራተኞች ስልጠና በሚል የትምህርት ፕሮግራም ተቋርጦ ስብሰባ እንዲገቡ በመደረጉ የቀሩት የድርጅቱ አባል ያልሆኑ 75 መምህራን በድርጊቱ በመናደድ ፣ በትምህርት ቤት የትምህርትን ክፍለ ጊዜ በማቃወስ የፖለቲካ ስብሰባ መካሄዱን ተቃውመው ወደ ቤታቸው ሄደዋል። ተማሪዎቹም አስተማሪ ስላጡ ወደየቤታቸው ለመሄድ ተገደዋል። በዚህም ሁኔታ የትምህርት ስራ ለሁለት ቀናት ተቋርጧል።ይህን ሁኔታ በመከተል በአካባቢው በሚገኙ ት/ቤቶች የሚያስተምሩ የወያኔ ደጋፊ ያልሆኑ መምህራን ተመሳሳይ እርምጃ በመውሰድ ተቃውሟቸውን አየገለጹ መሆናቸው ተረጋግጧል። መቀጠል ያለበት የትግል ስልት ነው።
ከተማሪዎች ጋር በተደረገው ስብሰባም ከተነሱ ጥያቄዎች መካከል በሌሎች አገሮች የስልጣን ዘመን የተገደበ ነው።እናንተ ግን ወደ ስልጣን ከወጣችሁ 23 ዓመታት ሆናችሁ። ስልጣናችሁን ልቀቁ፣ እናንተን አንመርጥም፣ በቃችሁ። የሕግ የበላይነት አለ ትላለችሁ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ከ6 ወራት በላይ እንዲሁም ሌሎችን ፍ/ቤት ሳታቀርቡ በእስር ማቆያታችሁ የተያዙ ሰዎች በአርባ ስምንት ሰአታት ውስጥ ፍ/ቤት የመቅረብ መብት አላቸው የሚለውን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ አይጻረርምዎይ? በትምህርት ቤት ተማሪዎችን በኢህአዴግ አባልነት ትመለምላለችሁ ፣ በህዋስ በአንድ ላምስት ታደራጃላችሁ፣ ትምህርት ቤት በማናቸውም ረገድ ከሃይማኖት ፣ ከፖለቲካ አመለካከቶችና ከባሕላዊ ተጽዕኖዎች ነፃ መሆን አለበት ከሚለው ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ አይጻረርምዎይ? ተቃዋሚዎች ይህን በት/ቤቶች እንዲያደርጉ ተፈቅዳላችሁዎይ?-----የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በማንሳትና ኢህአዴግ ይውደም!ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር! የሚል መፈክር በማሰማት ስብሰባው ያለምንም መግባባት በልዩነት

ከመጠናቀቁም በሻገር ተማሪዎች ለነሷቸው ጥያቄዎች የወያኔ/ኢህአዴግ ካድሬዎች መልስ መስጠት ተስኗቸው እንደነበር ለመራዳት ተችሏል።

ወያኔ/ኢህአዴግ ከአባላቱ ጋር በጥር ወር 2007ዓ.ም መጨራሻ ባካሄደው ስብሰባ ከአባላቱ በርከታ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ቀርበዋል። ከነዚህም ለተቃዋሚዎች መፈራረስ የኢህአዴግ እጅ አለበት ፣ ኢህአዴግ ዲሞክራሲ አለ ይላል ግን ያስራል፣ ይገርፋል፣ ይገድላል። ይህን እየፈጸማችሁ ከደርግ በምን ትሻላለችሁ? የአማራ ወጣቶች በሌሎች ክልሎች ተቀጥረው አይሰሩም? የሌሎች ክልሎች ወጣቶች ግን በአማራው ክልል እስከ መሾም ይደርሳሉ። የእኛ አገር የሕዝብ ተወካዮችና ሌሎችም ምርጫዎች ከሌሎች አገሮች ምርጫዎች ጋር እንዴት ይነጻጸራል? ለመንግሥት ሠራተኞች የተሰጠው የደመወዝ ጭማሪ ፍትሐዊ አይደለም። አርሶአደሩ ከይዞታ መሬቱ ያለበቂ ካሣ እየተፈናቀለ ነው ለዘለቄታው ምን ታስቦበታል? የድርጅት አባላት ድርጅቶቻቸውን ያማርራሉ ችግሩ ምንድነው? አየለ ጫሚሶና መሰሎቹ የኢህአዴግ ሽርጥ ለባሾች እንጂ ተቃዋሚ አይደሉም ---ወዘተ የመሳሰሉ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተሰጥተው ከመድረክ መሪዎች የተሰጡ ምላሾች ቁጣን በመቀስቀሳቸው ስብሰባው ያለምንም መግባባት ተጠናቋል።

በሌላ በኩል በመንግሥት መስሪያ ቤቶችም ሆነ በትምህርት ቤቶች በበጀት እጥረት የተነሳ ስራ ወደ መቆም የተቃረበበት ፣ ካድሬዎች ከምርጫ ጋር በተያያዘ በስብሰባ የተጠመዱበትና ፍርሃታቸው ከምንጊዜውም በላይ ገዝፎ እርስ በርስ አለመተማመን ደረጃ ላይ የደረሱበት ፣ ሰራተኛው ፊት ለፊት ስርአቱን እየሞገተ ጥላቻውን በግልጽ እያሳየና ለስርዓት ለውጥ ለሕዝባዊ እምቢተኝነት ራሱን እያዘጋጀ እንደሆነ ይታያል።

የኑሮ ውድነቱ፣ የስራ ዋስትና ማጣት ፣ የመብት ረገጣው፣ የመልካም አስተዳደር እጦት -----ያስመረራቸው መምህራን የተለያዩ የመብት ጥያቄዎችን በማንሳት ላይ ይገኛሉ።ከእነዚህ ውስጥ የሚጠቀሱ በደሴ ከተማ የሚገኙ የአንዳንድ ት/ቤቶች መምህራን ለተመሳሳይ ስራ ተመሳሳይ ክፍያ ይደረግ፣የመምህራን የዕድገት መሰላል ( Career Structure) በአንዳንድ ክልሎች ተሻሽሎ ተግባራዊ ሲሆን በሌሎች ክልሎች ለምን አይተገበርም ? የቤት አበል ( Housing allowance) ለምን ተግባራዊ አይሆንም? የቤት መስሪያ ቦታ ያለምንም ክፍያ በነፃ ልናገኝ ይገባል። የትምህርት ጥራትን እናረጋግጣለን እየተባለ በይድረስ ይድረስ በዘፈቀደ በለብለብ ለመህራንና ለሌሎች ባለሙያዎች ስልጠና እየተሰጠ ነው፣ ይህ በአስቸኳይ እንዲቆም እንጠይቃለን። የተሰጠው የደመወዝ ጭማሪ የኑሮ ውድነቱን ያላገናዘበ ስለሆነ እንደገና ማስተካከያ እንዲደረግበት የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት በየካቲት ወር 2007ዓ.ም መጀመሪያ ፒቴሽን ተፈራርመው ለሚመለከታቸው አካላት በማቅረብ ጥያቄዎቹ አስቸኳይ መልስ ካልተሰጣቸው የስራ ማቆም አድማ እንደሚያደርጉ አስታውቀዋል። ይህ በደሴ ከተማ መምህራን የተነሳው ጥያቄ በአገሪቱ የሁሉም መምህራን ጥያቄ፣ ከዚያም ባለፈ ባጠቃላይ የሠራተኞች ጥያቄ ስለሆነ ለተግባራዊነታቸው ዜጎች ሁሉ እንዲተባበሩና ትግሉን እንዲያግዙ በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ጥሪውን ያቀርባል።

በዚህ ጽሑፍ ወያኔ/ኢህአዴግ  መምህራንን ፣ ተማሪዎችንና የራሱንም አባላት በተለያዩ ጊዜያት ሰብስቦ ለማወያየት መሞከሩን አይተናል። በተለይ በመግቢያው ላይ  በተመለከቱት የመወያያ አጀንዳዎች ላይ በነቂስ ለመተቸት አንድ መድበል የሚወጣው ስራ ይጠይቃል። በጥቂቱ ቀንጨብ አድርገን ለማሳየት እንገደዳለን። ልማታዊ አስተሳሰብ ምንጩ ጥሩ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው። የፖሊሲው ቅኝት በአንድ ዘረኛ ፓርቲ ቁጥጥር በዋሉና ንብረትነታቸው የፓርቲው የሆኑ ኩባንያዎች ያለገደብ   ያለውድድርም ተጠቃሚዎች በሆኑበት ስርአት ፣ ሌሎች የግል ባለሐብቶች ወደዳር በሚገፉበት ሁኔታ አባባሉ ጉንጭ አልፋ ከመሆን አይዘልም። የህዳሴው መነሻና መድረሻ ሕዝብ በወጉ እንዲያውቀውና እንዲቀበለው ያልተደረገ በሂደቱም የጠራ አቋም ይዞ በፍላጎት ላይ በተመሰረተ ስሜት የማይሳተፍበት ፣ የጉልበት፣ የዕውቀት፣ የማቴርያል፣ የገንዘብ እገዛ እንዲያደርግ የሚያዘጋጁ ስነልብናዊ  ሁኔታዎች ባልተመቻቹበት ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ከየት ወዴት የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል።በዚሁ ላይ ዕድገት በተመጽዋችነት ፣ በርዳታና በብድር ውጤታማ የሆነበት አገር በ50 እና 60 አመታት አልታየም። በተለይ ኢትዮጵያን በመሰሉ የአፍሪካ አገሮች ያተረፈው ነገር ቢኖር የአምባገነኖችን ኪስ ማሳበጥና የአገዛዝ ጡንቻቸውን ማጠንከር ሆኗል። ስለዚህ በአገዛዝ ስር ያለ ሕዝብ የዕድገትና ሽግግር መለኪያው የአገዛዙን ከንቱ ውዳሴ ከማጉላት ውጪ የሚታይ አይሆንም።

ስለትምህርት ፖሊሲው ሰንካላነት፣ ስለካርኩሉም፣ ስለመምህራን ምልመላና ስልጠና ስለትምህርት ግብአቶች ጥራትና ተደራሽነት ችግር----በተለያዩ መግለጫዎች ለሕዝብ ለማሳወቅ ሞክረናል። ብዙ አገር ወዳድ ምሁራንም በተለያዩ ጊዜያት ስለትምህርቱ ውድቀትና ትውልድ ገዳይነት ትችት አቅርበውበታል።ሌላው ቀርቶ መምህራን  በነፃነት በሙያቸው ተደራጅተው ስለትምህርቱ ሂደት በተለይና ስለአገራቸው ጉዳይ ባጠቃላይ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዳያደርጉና ብሔራዊ ግዴታቸውን እንዳይወጡ በሚያግድ ፣በሚያደናቅፍና ማህበራትን በአንድ ፓርቲ ዕዝ በሚያስገባ ስርዓት "የተምህርት ሠራዊት ግንባታ" የሚል ርዕስ የተካተተበት አጀንዳ መምህራንን ለማደናገር ማቅረብ ቧልት በመሆኑ የወያኔ ስብሰባ ውሉ ጠፍቶበት መጠናቀቁ ታይቷል። ትምህርቱንና ትውልዱን የመግደል  የወያኔ ስልት ገና ከመነሻው 42 የዩኒቨርሲቲ ዕውቅ መምህራንን በማባረር አሳይቷል።አሁን በቅርቡም ሁሉቱን ብርቱ የዩኒቨርሲቲ መምህራን አባሯል። ስለትምህርቱ  ጥራትና ውድቀት ከተባራሪዎቹ አንዱ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ያለበቂ ዝግጅት፣ ብቃት ያላቸው  መምህራን ሳይኖሩ፣ የትምህርት ግብአቶች በሚፈለገው ደረጃ ሳይመቻቹ በየጨካው ዩኒቨርሲቲ መክፈት ምርታማ ዜጎችን የማያወጣና የአገሪቱን አንጡራ ሀብት እንደማባከን እንደሚቆጠር አመላክተዋል።ማን ያርዳ የቀበረ ፣ ማን ይንገር የነበረ እንዲሉ። ይህ ሕዝብን የማደንቆር ፖሊሲ አንድ ቦታ ካልቆመ

የትውልድ ግድያው ይቀጥላል። የትምህርት አፓርታይድ የተከለው ወያኔ ሕዝብን አደንቁሮ የመግዛት ኃይሉ እየጎለበተ ከመሔዱ በፊት ወላጆች፣ተማሪዎች ፣ ሌሎች የሕብረተሰቡ አካላት ለአሁኑና ለተተኪው ትውልድ ዕጣ ፋንታ መቆም ይጠበቅባቸዋል።
ለዚህ ነው መምህራን በየወቅቱ ፣ በየቦታው የተቃውሞ ድምጻቸውን እያሰሙ ያሉት። በራሳቸው ላይ ቤንዚን በማርከፍከፍ መስዋዕት የሆኑት። ጩኸታቸውን ኢትዮጵያውያን በያሉበት አስተጋብተው ትውልዱን ከድንቁርናና ከሞት እንዲታደጉ በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ጥሪውን በድጋሚ ያቀርባል።

ለስርዓት ለውጥ ትግሉ ይፋፋም!!
በትምህርትና በባለሙያዎች ላይ መቀለድ ያብቃ!!
ትምህርት የዕድገት መሰላል ነው! መወጣጫው አይፋለስ!!